https://chilot.me

፬/ በታክስ አስተዳደር አዋጅ፣ በገቢ ግብር አዋጅ እና በጉምሩክ አዋጅ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሐረጋት ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ለኮሚሽኑ በይግባኝ በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ እና ከጉዳዮቹ ጋር በተያያዘ አግባብነት ባላቸው ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ ይግባኝ</u>

4. <u>ይግባኝን ስለማቅረብ</u>

1/ ይግባኝ መቅረብ ያለበት በይግባኝ ባይ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ አማካኝነት ብቻ ነው፤

2/ ይግባኙ በጽሑፍ ሆኖ በይግባኝ ባይ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ ተፈርሞ በአካል ለኮሚሽኑ መቅረብ አለበት።

5. <u>የይግባኝ አቤቱታ ይዘት</u>

1/ ለኮሚሽኑ የሚቀርብ ይግባኝ በጽሑፍ ሆኖ ፡-

ሀ/ የይግባኝ ባዩን ስምና አድራሻ፣በወኪልና ሲሆን በይግባኝ ባይ የተሰጠውን የውክልና ሥልጣን እንዲሁም የተወካይ ስምና አድራሻ፣

ለ/ የታክስ መለያ ቁጥሩን፣

ሐ/ ይግባኙ መሠረት ያደረገባቸውን ዝርዝር ጉዳዮች፣ ይግባኝ የተመሰረተበት ፍሬ ነገር እና የህግ ጉዳይ ፣

መ/ ይግባኝ የቀረበበትን የግብር ውሳኔ የሰጠው አካል ለውሳኔው የሰጠውን ምክንያት እና የይግባኝ ባይ መቃወሚያ ፣

ሠ/ በማስረጃነት የሚቀርቡ ሰነዶች ፣በምስክርነት እንዲቀርቡ የሚፈልጋቸው ሰዎች ስምና አድራሻ እና የሚያስረዱለትን ጉዳይ በአጭሩ፣

ረ/ ሌሎች ለኮሚሽኑ ውሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን ጉዳዮች ፣
ማካተት አለበት።

2/ ይግባኝ ባይ ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው የሚላቸውን ማስረጃዎች ዝርዝርና የሚያስረዱለትን ፍሬ ነገር አጭር መግለጫ ከማመልከቻው ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት ።

https://chilot.me

17. <u>የኮሚሽኑ የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት</u>

1. እያንዳንዱ ችሎት አምስት አባላት የሚኖሩት ሲሆን ከኮሚሽኑ አባላት ሦስቱ ሲገኙ ችሎቱ የተሟላ ይሆናል።
2. ኮሚሽኑ በቀረቡለት የይግባኝ ጉዳዮች ላይ በድምጽ ብልጫ ውሳኔ ይሰጣል።
3. ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. በሃሣብ የተለየ የጉባኤው አባል የሀሳብ ልዩነቱን በውሳኔው ያሰፍራል።

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

18. <u>ሌሎች ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ህጎች</u>

የታክስ አስተዳደር አዋጅ፣የጉምሩክ አዋጅ እና የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

19. <u>የተሻሩ አሰራሮችና መመሪያዎች</u>

ይህ መመሪያ ተፈፃሚ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ማንኛውም ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን አሰራር ወይም መመሪያ ተሽሯል።

20. <u>መመሪያው ተፈጻሚ ስለሚሆንበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ-----/---/2011

አብይ አህመድ (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Tax Appeal Commission

ቁጥር ታ.ይ.ኮ/ጽ.ቤ 128/11
ቀን 30/07/11

ለገቢዎች ሚኒስቴር
ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>
ለሬጅስትራር
<u>ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን</u>

**ጉዳዩ:- <u>ይግባኝ የሚቀርብበት የፀደቀ ቅጽ ስለመላክ</u>**

በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 88(5) የኮሚሽኑ ፕሬዚደንት ይግባኝ የሚቀርብበት የፀደቀ ቅጽ አዘጋጅቶ እንደሚያቀርብ ይደነግጋል። በዚሁ መሰረት ይግባኝ ማቅረቢያ ቅጽ 2 ገጽ በዚህ ደብዳቤ ሸኚነት እየላክን በዚሁ መሰረት ተግባራዊ እንዲደረግ እስታውቃለሁ።

ከሠላምታ ጋር

**ግልባጭ**
ለክቡር ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
<u>አዲስ አበባ</u>

ራዕያችን - ሕግን መሠረት ያደረገ ፍትሐዊ የግብር አስተዳደር ሥርዓት ማስፈን ነው!!

https://chilot.me

# የፌደራል የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን

የማስረጃ ዝርዝር

ሀ/ የሰነድ

1.

2.

3.

የሚያስረዱት ጉዳይ ባጭሩ፡- ------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------::

ለ/ የሰው

| ስም | አድራሻ |
| --- | --- |

1.

2.

3.

የሚያስረዳዉ ጉዳይ ባጭሩ፡- -----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------::

የቀረበው ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 92 መሰረት እውነት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ይ/ባይ(ተወካይ) ስም------------------

ፊርማ---------------------------------